# እኔም ትግሬ ነኝ

ከበልጅግ አሊ

የሁለተኛው የአለም ጦርነት ያደረሰው ዘመን የማይሽረው ጥፋት ብዙ የተነገረለትና የተፃፈበት ነው።ከጥፋቶቹ እኩል ደግሞ እፁብ ድንቅ የሆኑና በዓለም ታሪክ ላይ በወርቅ ቀለም የተፃፉ ተግባሮች ተከናውነዋል።የዛሬው ጽሁፌ ስለሁለተኛው አለም ጦርነት ለመፃፍ ባይሆንም ለፅሁፌ መነሻ አጋዥ ነጥብ እንዲሆንልኝ ያ የጥፋት ዘመን ማዕበል በሰፈነበት ወቅት በብዛትና በስፋት ተደርጎ ቢሆን ኖሮ የጦርነቱን የመጨረሻ ውጤት ይቀየር ነበር ብዬ የምገምተውን በጎ ተግባር ላንሳ ብዬ ነው።

ወቅቱ የናዚ ሂትለር ክንድ መላ አውሮፓን በቁጥጥሩ ስር አድርጎ በአውሮፓ ለሚገኙ አይሁዳውያን << <u>የመጨረሻ መፍትሄ ለአይሁዳውያን ጥያቄ</u> >> በሚል አይሁዳውያንን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት በአውሮፓ በተለያዩ ቦታዎች እስር ቤቶችንና በመርዝ የመግደያ ክፍሎችን አቋቁሞ ጭካኔ የተሞላበት ኢ- ሰባዓዊ ድርጊት የሰፈነበት 1941 ዓ.ም ነበር። በአውሮፓ ውስጥ በተለያዩ አገሮች ይገኙ የነበሩ አይሁዳውያን እየተሰበሰቡ በእስር ቤት ይታጎሩም ነበር። እንደሚታወቀው ሂትለር አይሁዳውያን ከሌላው ሕዝብ ነጥሎ ለመምታት እንዲያመቸው እያንዳንዱ አይሁዳዊ ባለ ስድስት ጫፍ የሆነውን የንጉስ ዳዊትን ኮኮብ ክንዱ ላይ እንዲያሰር ትዕዛዝ አውጥቶ ነበር።

ይህንን አንድ ዘርን ለማጥፋት የተዘጋጀውን አረመኔያዊ ተግባር በመቃወም በአውሮፓ በተለያዩ ቦታዎች እንቅስቃሴ ቢደረግም በዴንማርክ የተደረገው ግን እስከ አሁን ድረስ በክብር ቦታ ተፅፎ ይገኛል። ይህንን የናዚዎች ትዕዛዝ ዴንማርክያውያን በመቃወም <u><<እኔም አይሁዳዊ ነኝ>></u> በሚል መርህ የናዚን ኃይል ከመጤፍ ባለመቁጠር የ7500 የዴንማርክ አይሁዳውያንን ከሞትና ከእስራት አድነዋል።

የዴንማርክ ሕዝብና የወቅቱ ንጉስ ክርስቲያን አስረኛ ይህንን የናዚ ትዕዛዝ በመቃወም ያደረጉት ትግል እስከ አሁን ድረስም ይሁን ወደፊት በታሪክ ፊት ሲያስመሰግናቸው ይኖራል። ንጉስ ክርስትያን አስረኛው በክንዱ ላይ የንጉስ ዳዊት ኮኮብን አድርጎ በፈረስ በዴንማርክ ዋና ከተማ ኮፐንሃገን ውስጥ ይዘዋወራል ተብሎ ስለተወራ መላውም የዴንማርክ ህዝብም እኛም አይሁዳውያን ነን በማለት የንጉስ ዳዊትን ኮኮብ በማድረግ የሂትለር እኩይ ምግባር ማደናቀፍ ችለዋል።

ዴንማርካውያን አይሁዳውያንን በመደበቅና በወቅቱ በናዚዎች ባልተያዘችው ስውዲን በመላክ ታላቅ የሆነ ደግነትን የተላበሰ ጀግንነትን አሳይተዋል። በ1945 ዓ. ም. በጦርነቱ ፍፃሜ ወቅት በአውሮፓ 10 ሚሊዮን ከነበረው የአይሁዳውያን ቁጥር ከግማሽ ያነሰ ብቻ ነበር የተረፈው። ይህ የተደረገ ተመልሶ ሊስተካከል የማይችል ለሰው ልጅ በታሪካዊ ጠባሳነት ዘወትር የሚጠቀስ ምዕራፍ ነው። እንዳይደገም ምን ማድረግ ይኖርብናል? ይህንን ጥያቄ ሁላችንም ልናስብበት ይገባል።

ታዲያ ይህንን ታሪክ ለምን አመጣኸው ልትሉኝ ትቻላላችሁ። አዎ የረባ ምክንያት ሰላለኝ ነው። ሰሞኑን ወያኔን በመቃወም ስም በውጭ ተሰባስቦ በሚገኘው ሃይል ውስጥ በዘረኝነት፣ በጠባብነት አርማ ስር የተወሰነ ግለሰቦች የወያኔን ከስልጣን ለማውረድ አዲስ የትግል ስልት ጀምረናል በማለት በየቦታው ሲደሰኩሩ ስለሰማሁ

ነው። እነዚህ ኃይሎች አንድን ዘርን በመቃወም ትግል እንዲጀመር ጥረት እያደረጉ ናቸው። የተሰጠው ምክንያት 50 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ በአራት ሚሊዮን ትግሬዎች ሊበደል አይገባውምና 50 ሚሊዮኑ ከእነርሱ መለየት አለበት የሚል ቅስቀሳ ተጀምሯል።ቅስቀሳው በመቀጠልም ሌላው ዘር ትግሬዎችን ከአካባቢው ማስወጣት አለበትም በሚል በየፓልቶኩ አደገኛ የሆነውን ቅስቀሳቸውን ተያይዘውታል። ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛትነት ነው የተያዘችው የሚሉም ምሁራን ነን ባዮችም ብቅ ብለዋል።አንዳንዶቹ እንዲያውም አልፈው ተርፈው ወደ ድርጅትና መንግስትነት ለመለወጥም ጥረት እያደረጉ ነው።

ብዙዎቻችሁን ሊያስገርም ወይም ሊሆን አይችልም ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ ይችላል። ግን እየሆነ ያለ በመሆኑ ነገሩን በቀላል የምንመለከተው አይደለም። እንደውም ገና ከመጀመሩ ፓልቶኮችን በጥብጧል ፣ የፆታ ድርጅቶችን ከፋፍሏል። እንዳንድ የዋሆችን አሳምኗል።

በአለም ላይ በተለያየ ግዜ የተነሱ ፋሽሽቶች ፣ ዘር ያጠፉ አረመኔዎች ፣ ሁሉም እንደዚህ አይነት ጥያቄዎችን በማንሳት በለስ ሲቀናቸው ወደ ስልጣን ሲደርሱ ታይተዋል። በእንደዚህ አይነት መፈክር በመጠቀም ነው ወያኔ ስልጣን ላይ የወጣውና ኢትዮጵያን በማይገመት ፍጥነት ወደጥፋት የወሰዳት። ስልጣን ላይ ለመውጣት ብቻም ሳይሆን ለመቆየትም የቻለው አንድን ዘር እንደጥፋተኛ በመመደብ መሆኑ የታወቀ ነው።

ዛሬ እነዚህ እንደ ሞኝም እንደ እብድም እየቆጠርን የምናልፋቸው ግልገል ፋሽሽቶች ስልጣን ላይ ደርሰው ጭፍጨፋ ሲጀምሩ እኛ ገና በእራሳችን ላይ እየሳቅን ሊሆን ነው። ያልተማሩ ወታደሮች የት ይደርሳሉ ሲባል ነው ደርግ አንድ ትውልድ ጭጭ ያደረገው። ወያኔ ምን ይሆናል ብለን ተቀምጠን ነው ስልጣን ላይ ደርሶ የበደኖን ጭፍጨፋ ያካሄደው።

ዛሬ እነዚህ በፀረ ወያኔ ሳይሆን በፀረ ትግሬ የተሰባሰቡ ግለሰቦች ፣ ከግለሰብነት አልፈው የድርጅት ሕልውና ይዘው ለመንቀሳቀስ እየሞከሩ ነው።የሚቀጥለው አስደናቂ ተግባራቸው ደግሞ የስደት መንግስት የሚል እንደሚሆን የሰሞኑ እንቅስቃሴያቸው ግልፅ አድርጎታል።

ታዲያ አሁን የወያኔ ተቃዋሚዎች ከምንግዜውም ይበልጥ በተከፋፈሉበት ወቅት ብቅ ማለታቸው የግለኝነት አጀንዳቸውን ለማራመድ ነው? ወይስ እነዚህ ግለሰቦች የወያኔን አላማ በስውር የሚያስፈፅሙ በበጎች ውስጥ የተሰማሩ ተኩላዎች ናቸው? መልሱን የኢትዮጵያ ሕልውና ለሚያንገበግበው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እተዋለሁ።

የድርጅቶችን ድክመት እያወሱ ትግሉን << <u>አክቲቪስቶች</u> >> ይምሩት በሚል መፈክር በወያኔ የተከፋውን ህዝብ << <u>ጠላትህ ትግሬ ነው</u> >> በማለት ድጋፍን ለማግኘት እየሞከሩ ነው ። በለስ ከቀናቸው ፣ እንደ ኤርትራ መንግስት አይነት የሚረዳቸው ካገኙ ፣ ከወያኔ ፣ከደርግ ባልተሻለ ሁኔታ የንፁሃንን ደም በማፍሰስ ወደ ስልጣን ኮርቻ ከመውጣት የሚያግዳቸው ነገር አይኖርም።ቅስቀሳቸው የሚሆነው <<<u>የትግሬ መፍትሄ</u> >> ብለው እንደናዚዎቹ በአካባቢያችሁ ያሉትን ትግሬዎች ሁሉ ጨርሱ የሚል መፈክር ነው። ይህንን ዕቡይ ቅስቀሳ ሳያገናዝብ ወያኔ በበደኖ እንዳደረገው ሁሉ

በወያኔ ጥላቻ ላይ ብቻ በመመርኮዝ በአንድ ዘር ላይ ለሚደርስው ጥፋት አሁኑኑ ካላስቆምነው እያንዳንዳችን ተጠያቂዎች ነን።

ዛሬ በአለም ላይ የተሰራጩት እነዚህ ዳግማዊ ወያኔዎች በትግሬ ሳይሆን በሌሎች ዘሮች ስም ወደ ስልጣን ለመድረስ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። በወያኔ ላይ የተጠራውን ኢኮኖሚዊ ማዕቀብ ለፀረ ትግሬ መፈክራቸው ለማድረግ ጥረት ላይ ናቸው።ግባቸው ላይ ለመድረስም የተለያዩ ዕኩይ ስልቶችን በየአቅጣጫው ሰንዝረዋል። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል ቀደም ብለው የተቋቋሙ ድርጅቶችን ይኮንናሉ፣ ሃሳባቸውን ያልተቀበሏቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ያጥላሉ። የድርጅቶችን የውስጥ መከፋፈልን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ያንን በመጠቀም ደጋፊ ለማግኘት ይሯሯጣሉ። ዛሬ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ውስጥ ነች ብለው የሚቀሰቅሱ አሉ።ማነው ቅኝ የያዛት? ቅኝ ገዢው ይውጣ ከተባለ ወዴት? ስለዚህ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ገና ብዙ ያልተጠና የተስፋ ቆራጮች መፈክርና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚከት ከወያኔ የውስጥ ለውስጥ የጥፋት መረብ ያልተለየ በመሆኑ በቀላሉ ማየት አያስፈልግም።

ወያኔ ደግሞ ደጋፊዎቹን ይህንን ሁኔታ እየነገረ እያስፈራራ ስልጣን ላይ ተጣብቆል። ወያኔ የዘር ካርዱን አሁንም ወደ ፊትም ይጠቀምበታል ። ስለሆነም ይህንን አይነት ግልገል ዘረኝነትን የክፉ ስራ ማስፈጸሚያ ስልቱ ነውና ይወደዋል። የጸረ ወያኔውን ትግል ስለሚያዳክምለት፣ ተቃዋሚዎቹን ስለሚከፋፍላቸው በውስጥ ገንዘብ እየሰጠ ፣ መሬት እያከፋፈለ፣ የሚበረታታው እሱው እራሱ ነው ። ፀረ ትግሬ የሆነ እንቅስቃሴ ጸረ ወያኔ የሆነውን የወያኔ አባላትን ተጠያቂ የሚደርገውን ትግል ወደ ጅምላ ተጠያቂነት ስለሚሸጋግርለት ይደግፋዋል።

ግላዊ ፍላጎታቸውን ከሃገርና ከወገን ፍላጎት በማስቀደም ይህንን ክፉ ዓላማቸውን የሚያስችል ግዜ ጠብቀው የተነሱብንን ግልገል ዘረኞች ምኞታቸው እንዳይሳካ ሁላችንም አቁሙ ማለት ይኖርብናል። ስለኢትዮጵያ ሀገራችን ሕልውና እና ስለ ሕዝቧ ሰቆቃ ስንል ዛሬ ሁላችንም ተነስተን እንደ ዴንማርክ ሕዝብ እኛም ትግሬዎች ነን ብለን ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት አስቁመን በታሪክ ውስጥ የማያልፍ ስም ልንተው ይገባል። ዛሬ ይህንን ዘረኛ እንቅስቃሴ ከአሁኑ ማስቆም ካልቻልን ወደፊት ለሚፈጠረው ክፍፍል እልቂት አስተዋፅኦ ማድረጋችንን እያሰብን ከሞራል ተጠያቂነት ለመዳን የምንችለውን እናድርግ ።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ።

ጥቅምት 2001